# <u>መንግስትን ህዝባዊ አመኔታ የሚያሳጡ ቁልፍ ችግሮች</u>

**ኢዛና ዘመንፈስ 12-30-17**

የእያንዳንዱን ሀገር መንግስት በሚመራው ህዝብ ዘንድ አመኔታ እንዲያጣ ሊያደርጉት ስለሚችሉ መሰረታዊ ምክንያቶች ለማስረዳት የግድ የፖለቲካዊ ሳይንስ ምሁር ሆኖ መገኘት አይጠበቅብንም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ በየትኛውም ሀገር ውስጥ ፖለቲካዊ ስልጣን የመጨበጥ ዕድል በገጠማቸው ኃይሎች አማካኝነት ከሚቋቋም የመንግስት አካል ህዝቡ ምን እንደሚጠብቅ በውል ይታወቃልና ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የዴሞክራሲ ጭላንጭል ባልደረሰባቸው ሀገራት ውስጥ ፖለቲካዊ ስልጣኑን የጨበጡ አምባገነናዊ መንግስታት ጭምር፣ ከሚመሩት ህዝብ ጋር የገገርና ተገገር ቅቡልነትን በሚያመለክት ይሁንታ ላይ የሚመሰረት መተማመኛ ይኖራቸው ዘንድ ግድ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ እኔም ለዚህ ነው ጉዳዩን ለመረዳት የተለየ እውቀት አይጠይቅም ማለቴ፡፡

ለማንኛውም ግን ይህን መሰረተ ሃሳብ ያነሳሁት ያለምክንያት አይደለም፡፡ ይልቅስ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትመራበትን የፌደራል ስርዓት ህዝባዊ አመኔታ በማሳጣት ረገድ ትርጉም ያለው አሉታዊ ተፅእኖ እያሳደሩ ስለመሆናቸው የሚገመቱ አንዳንድ ተጨባጭ ችግሮችን የሚያመላክቱ ነጥቦች እያነሳን ብናይ ለመፍትሔ ፍለጋ ይበጅ ይሆናል የሚል እምነት ስላለኝ እንጂ፡፡ እንግዲያውስ አሁን በቀጥታ ወደ ዋናው የጽሑፌ ማጠንጠኛ ርዕሰ ጉዳይ እንለፍና መላው የሀገራችን ህዝቦች ፈርጀ ብዙ መስዋዕትነት ካስከፈላቸው የዘመናት ትግል በኋላ የተቀዳጁት ድል ድምር ውጤት ሆኖ ሳለ፣ ግን ደግሞ ተገቢ ዋጋ የተሰጠው ስለማይመስለው ህብረ ብሔራዊ ፌደራሊዝማችን ጠቀሜታ መነሳት ይኖርባቸዋል የምላቸውን መሰረታዊ ነጥቦች ለመመልከት እንሞክር፡፡ ስለሆነም ፌደራላዊት፣ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የምትመራበትን ሕገመንግስታዊ ስርዓት ህዝባዊ አመኔታ የሚያሳጣ ተግባር በመፈፀምና በማስፈፀም ረገድ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱ አካላትን ነው የማስቀድመው፡፡

እናም ከዚህ አኳያ፣ ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ያስቆጠረው፣ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ፣ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት የሚገባውን ያህል ህዝባዊ አመኔታ እንዳያገኝ ያደረገ አሉታዊ ሚና ተጫውተዋል የሚባሉትን ዋና ዋና አካላት በሶስት ከፍለን ልንመለከታቸው እንደምንችል ይሰማኛል፡፡ ይህን ስልም ደግሞ፣ ገና የደርግ ውድቀት መበሰሩን ተከትሎ በተጀመረው የተቃውሞ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ስር ነቀል የስርዓት ለውጥ ሂደቱን ተቀባይነት

ለማሳጣት ያለመ ተራ ማጥላላትን መሰረት ያደረገ ፕሮፖጋንዳዊ ዘመቻ ላይ በመጠመድ የሚታወቁትን የትምክህት ኃይሎችና እንዲሁም ደግሞ የጠባብ ብሔርተኛ ቡድኖች በመጀመሪያው ረድፍ እስቀምጠን፤ ከዚያም የነዚህ ሁለት ተቃራኒ የአስተሳሰብ ጽንፎች አሉታዊ ጫና ድምር ውጤት መገለጫዎች የሆኑ ሌሎች አካላትን ማስከተል ተገቢነት ሊኖረው እንደሚችል መጠቆሜ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም "የመንግስት ሚዲያዎች" እየተባሉ የሚጠሩት የህዝብ መገናኛ ብዙኃንና ኃላፊነት የማይሰማቸው የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች፤ ወይም ሹማምንት፤ ስርዓቱን ህዝባዊ አመኔታ በማሳጣት ረገድ እንደየቅደም ተከተላቸው የሚገለጽ አሉታዊ ሚና ይጫወታሉ ባይ ነኝ እኔ፡፡

ስለሆነም በድህረ ደርግ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከፈተውን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ፤ ገና ከመነሻው ጀምሮ "ውግዝ ከምዓሪ ወስ" እንደማለት በሚቃጣው ጭፍን ስሜታዊነት ከማጥላላት ቦዝነው የማያውቁት ፅንፈኛ የተቃውሞው ጎራ ፖለቲከኞችና እነርሱው እንደልሳን የሚጠቀሙባቸው የግሉ ፕሬስ ሚዲያ ውጤቶች፤ የሚታወቁበት ኢ-ሚዛናዊ ዘገባ እንደ አንደኛ ደረጃ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጣሪ አካላት ሊወሰዱ የማይችሉበት ምክንያት የለም የሚለው ነጥብ አንደተጠበቀ ሆኖ፤ ለእነዚህ የለየላቸው የፌደራል ስርዓቱ ተፃራሪ ኃይሎች ፕሮጋንዳዊ ዘመቻ ተቀባይነት የማይናቅ ድርሻ የሚያበረክተውን ክፍተት በማስከተል ረገድ ደግሞ፤ ራሱን ኢህአዴግ መራሹን መንግስት ወክለው የሚተውኑ የስራ ኃላፊዎችና አዝማሪዎቹ መገናኛ ብዙኃን ናቸው ተጠያቂዎች እላለሁ፡፡ ከዚሁ የግል ምልከታዬ የሚመነጭ እምነቴን የሚያንፀባርቅ ሃሳብ ላይ በተመሰረተ መሰል ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥን አስተያየት ከመሰንዘር የቦዘንኩበት አጋጣሚ እንደሌለም እርግጠኛ ነኝ፡፡ ይሁን እንጂ አዲሲቷ ፌደራላዊት፤ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የምትመራበትን ሕገ መንግስታዊ ስርዓት በመላው የብሄር ብሔረሰብ ህዝቦቿ ፍላጎትና ይሁንታ ላይ ያልተመሰረተ ለማስመሰል ያለመውን ተአማኒነት የማሳጣት አሉታዊ ተፅዕኖ የመፍጠር ፕሮፖጋንዳዊ ዘመቻ በማቀነባበር ተግባር የተጠመዱት አካላት የሚያደርጉት ፈርጀ ብዙ አፍራሽ እንቅስቃሴ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሲመጣ በመስተዋሉ ምክንያት፤ እኔም ርዕሰ ጉዳዩን ደጋግሜ ለማንሳት ተገድጃለሁ፡፡

ደግሞስ መላው የሀገራችን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለህብረብሔራዊ የጋራ ማንነታቸው ዕኩል ዕውቅናን ከሚሰጥ ዕርስ በርስ መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነትን ለመገንባት ይበጃል በሚል ተስፋ መክረው ዘክረው ያጸደቁትን ፌደራላዊ ሕገ መንግስት፤ እንደተራ ነገር ቆጥረን በስልጣን ናፋቂዎቹ ፅንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች የቀለም አብዮት እንዲናድ መፍቀድ ይኖርብናል

እንዴ ወገኖቼ? እንደኔ እንደኔ ግን፤ ህብረ ብሔራዊው የፌደራል ስርዓት ምን ያህል ለማመን እንኳን የሚያዳግት ፈርጀ ብዙ መስዋዕትነትን በጠየቀ የዘመናት ትግል እንደመጣ እናውቅ ይመስል፤ በጥገኛ ኃይሎች ቡድናዊ የሁከትና የነውጠኝነት ተግባር ምክንያት እንዲቀለበስ የሚያደርግ ዕድል መስጠት የለብንም፡፡ ይህን ስልም ደግሞ ከላይ የተጠቆሙትን የኢፌድሪ ሕገ መንግስት በርካታ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከምትታወቅበት የብሔር ብሔረሰብ ህዝቦቿ ብዝኃነት አኳያ ጠቀሜታቸው የጎላ ጠንካራ ጎኖች ያሉትና እንደስርዓት ድክመቶቹን እንዲያርም ሊነገረው እንደሚገባ የምናምን ዜጎች ሁሉ፤ ስርዓቱን አመኔታ የሚያሳጣ ኢ-ምክንያታዊ ውግዘት ላይ ከተመሰረተ የጭፍን ተቃውሞ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በሚመነጭ ጅምላዊ ፍረጃ ማጥላላትን የሚያዘወትሩ ወገኖች ልክ እንዳልሆኑ መናገር ይጠበቅብናል ማለቴ እንደሆነ ልብ ይባልልኝ፡፡

ይልቁንም ደግሞ ህዝቡ የመንግስት አካላት እንደሆኑ አድርጎ በሚቆጥራቸው አንዳንድ ኃላፊነት የማይሰማቸው ወገኖች ዘንድ በሚስተዋል ለስርዓቱ ታምኖ ያለመገኘት ችግር ምክንያት እየተፈጠረ ያለው ቅሬታ እንደሀገር ሊያሳስበበን የሚገባና አፋጣኝ መፍትሔ የሚሻም ጭምር ሆኖ ሳለ፤ ግን ደግሞ እንብዛም ልብ ሳይባል መቆየቱን የሚያመለክት ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ደግሞ አንድን መንግስት በሚመራው ህዝብ ዘንድ አመኔታ ከማሳጣት አኳያ ከለየላቸው ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ይልቅ ራሱን መስለው እየታዩ በስሙ የሚያገኙትን ስልጣንና እንዲሁም የራስ ኃላፊነት ተጠቅመው ህዝቡን ለሚያስመርር አስተዳደራዊ በደል ማስፈፀሚያ ሲያውሉት የሚያስተውሉት ምግባረ ብልሹ አካላት ናቸው ህብረተሰቡን የሚያሳዝኑት፡፡ እንጂ ጽንፈኞቹ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና አባላቶቻቸውማ ቀድሞውንም የስርዓቱን በጎ ገጽታ ጥላሸት ከመቀባት ያለፈ ተግባር ይኖራቸዋል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

ሌላው የኢፌድሪ መንግስት ህዝባዊ አመኔታን እንዲያጣ በማድረግ ረገድ የማይሰተባበል አሉታዊ ድርሻ ያለው የስርዓቱ አንዳንድ አካል ደግሞ “መንግስታዊ ሚዲያዎች” የሚል ጥቅል ስያሜ የሚሰጠው የመገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የመንግስት በመባል የሚታወቁት አብዛኞቹ የሀገራችን መገናኛ ብዙኃን ውስጥ ስለሚስተዋለው ዘርፉን “አዝማሪ ሚዲያ” ተደርጎ እንዲወሰድ ያደረገ ሚዛናዊነት የሚጎድለው ኢ-ተአማኒ ዘገባ እንደቀልድ የሚነገሩ የህዝብ አስተያየቶችን ለሰማ ሰው እውነታውን በተሻለ መልኩ መረዳት አይከብድም፡፡ ለአብነት ያህልም “የኢህአዴግ መራሹ መንግስት ሚዲያ ከሚናገረው አምኖ መቀበል የሚቻለው ሰዓቱን ብቻ ነው” እስከ ማለት የሚደርስ ቅሬታ አዘል አስተያየት የሚሰጡ አንዳንድ ሰዎች አሉ፡፡ ምንም እንኳን ይሄን ዓይነቱ አስተያየት ከበስተጀርባው፤ የትምክህትና የጠባብ

ብሔርተኝነት ጽንፈኛ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ የሚገለጽበት የተቃዋሚዎች ጭፍን ማጥላላት ላለመኖሩ ማረጋገጫ የለንም ሊባል ቢችልም፤ ግን ደግሞ ሙሉ በሙሉ እውነትነት የለውም ብሎ መደምደምም ተገቢ ሆኖ አይሰማኝም፡፡

ስለዚህ መንግስትን የጠቀሙ እየመሰላቸው፤ ያልተሰራውን ሁሉ ተሰርቷል እስከ ማለት የሚደርሱ መገናኛ ብዙኃን ስርዓቱን ህዝባዊ አመኔታ በማሳጣት ረገድ ስለኢህአዴግ መራሹ መንግስት በጎ ገፅታ ትንፍሽ ሲሉ ከማይደመጡት የግል ፕሬስ ሚዲያ ውጤቶች የማይተናነስ (ምናልባትም የበለጠ) አሉታዊ ሚና ይጫወታሉ ብለን ብናጠቃልል ከእውነታው መራቅ አይሆንብንም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ "የመንግስት ሚዲያዎች ከሚናገሩት ውስጥ አምኖ መቀበል የሚቻለው ስለሰዓቱ ትክክለኛነት ብቻ ነው" የሚለውን የጽንፈኛ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ጭፍን ውግዘት እውነትነት ያለው የሚያስመስል አሉታዊ አንድምታው የትየሌለ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላልና ነው፡፡ አንዳንድ በኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ችግር ምክንያት መንግስታዊ የስራ ኃላፊነታቸውን ተጠቅመው ህዝቡን በአስተዳደራዊ በደል ሲያማርሩት የሚስተዋሉ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና ሹማምንቶችም ከጽንፈኞቹ ተቃዋሚ ቡድኖች ይልቅ የፌደራል ስርዓቱን አመኔታ እንዲያጣ አድርገዋል፤ እያደረጉም ናቸው፡፡ እንዲሁም ደግሞ የማይፈፀም ዕቅድ ነድፈው ስለአማላይ ውጤቱ የሚያወሳ ተስፋቸውን በማያሻማ ማብራሪያ ለህብረተሰቡ ከገለፁ በኋላ አስቀድመው የተናገሩለት የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አጀንዳ ከምን እንደደረሰ እንኳን ስለመግለፅ አስፈላጊነትም ጭምር የሚዘነጉት መስለው የሚታዩ የመንግስት አካላት፤ ስርዓቱ እንደስርዓት በዋሾነት እንዲፈረጅና በዚያው ልክም ህዝባዊ አመኔታ እያጣ እንዲሄድ ከማድረግ አኳያ ሚዛን የሚደፉ አሉታዊ ሚና ስለመጫወታቸው ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡

ስለሆነም እንደኔ እንደኔ የፌደራል ስርዓቱን ሲፈታተኑት ከሚስተዋሉ የቅልበሳ አደጋዎች በስተጀርባ ፅንፈኞቹ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች፤ ከሀገር ቤት እስከ ባህር ማዶ ድረስ የተዘረጋ መረባቸውን ተጠቅመው የሚፈፅሙትና የሚያስፈፅሙት ፈርጀ ብዙ ደባ የመኖሩ ጉዳይ ባያከራክርም ቅሉ፤ ዋነኛው መፈታት ያለበት ቁልፍ ችግር ግን የራሱ የመንግስት አካላት በህዝቡ ላይ ሲቀልዱ የሚታዩበት አግባብ ነው፡፡ ለዚህ ጠጣር አስተያየቴ መነሻ ምክንያት ስለሆኑኝ ተጨባጭ የፌደራሉ መንግስትና እንዲሁም ደግሞ የክልላዊ መስተዳደሮች የስራ ኃላፊዎች መታረም የሚገባቸው ድክመቶች፤ አንድ ሁለት ሶስት … እያልኩ በዝርዝር ማብራሪያ አስደግፌ ማቅረብ እንደምችል ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡ ስለዚህም፤ አሁን ላይ ከተለመደው በተለየ መልኩ የራሱን ውስጣዊ ድክመቶች የመፈተሽና

ሀገራችንን መስቀለኛ መንገድ መሀል እንድትቆም ላደረጓት ወቅታዊ የጋራ ችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ የሚያመጣ አቋም ለመያዝ ያለመ ጥልቅ ግምገማ እያካሄደ ስለመሆኑ የሚነገርለት የገዢው ፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፤ በዚህ መጣጥፍ ላይ ለማመልከት የተሞከሩትን የመንግስት አካላት ደካማ ጎኖች ስለማረም አስፈላጊነት ልብ እንዲልልኝ እጠይቃለሁ፡፡ አለበለዚያ ግን አሁንም የስርዓቱን አሳሳቢ አደጋዎች ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀልበስና የፀረድህነት ትግሉን ጉዞ አጠናክሮ ለማስቀጠል የሚያስችለንን ዘለቄታዊ የመፍትሔ አቅጣጫ በማስቀመጥ ረገድ በኢፌድሪ መንግስት የሚደረገው ያላሰለሰ ጥረት የሚጠበቀውን ያህል አመርቂ ውጤት ላያመጣ ይችላል ብለን ብንገምት "ጨለምተኝነት ነው" የሚያሰኝ አይሆንም፡፡ በተረፈ ለዛሬ እዚህ ላይ አብቅቻለሁ፡፡